# የትግራይን ህዝብ ለቀቅ - የህወሃት/ኢህአዴግን መሪዎች ጠበቅ

ዶ/ር ነገደ ጎበዜ

የብሄር ጥያቄን አስመልክቶ ከአሉት እውነታዎች እየተነሳን አንድ የጋራ የሆነ መደምደሚያ መድረስ አቃተን እንጂ ዛሬ በሃገራችን ማንም አሌ ሊላቸው የማይችል ግልፅ የሆኑና በተጨባጭ አሃዞች ተመርኩዘው ሊደረደሩ የሚች ሉ ሃቆች አሉ። በሃገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ አንድን ብሄር እወክላለሁ እያለ የሚቀጥፍ በዚህ ብሄር ስም የተደራጀ አክራሪ ቡድን የሃገሪቱን መንግስት፣ የጦር፣ የፖሊስ፣ የፀጥታ ተቋማትና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዋን በሙሉ ቁ ጥጥሩ ውስጥ ያደረገበት ሁኔታ ውስጥ ነን። በሃገራችን ታሪክ አሁንም ለመጀመሪያ ጊዜ ህዝባችን ይህ የተጫነበት ስ ርአት "በአንድ ብሄር ለአንድ ብሄር" የተዋቀረ ስርአት ነው ብሎ እንዲያምን በግልፅ እየተገፉ ያለበት ሁኔታ ውስጥ እ ንገኛለን። አሁንም በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ እፍኝ የማይሞሉ የአክራሪዎች ጥርቅም በህዝብ ላይ ለሚፈፅመ ው ወንጀል እንዳለ አንድን ብሄር አባሪ ተባባሪ አድርጎ ለማቅረብ ይህ ነው የማይባል የስውርና የይፋ ስነልቡናዊና የፖለ ቲካ ጦርነት ሲያካሂድ እየታዘብን ነው።

የግንቦት 7 ንቅናቄ በአለፈው ሰሞን ይፋ ያደረገው በኢትዮጵያ ሰራዊት ውስጥ የትግራይ ተወላጆች የማያወላዳ የበላይነት ቦታ መያዛቸውን የሚያሳይና ብዙ በማነጋገር ላይ የአለ ሰነድ ከነዚህ ተጨባጭ ሃቆች በመጀመሪያ የጠቀስ ኩትን ማለትም "አንድን ብሄር እወክላለሁ እያለ የሚቀጥፍ" የአክራሪዎች ቡድን ሃገራችንን እየተቆጣጠረ መሆኑን በተ ጨባጭ መረጃ የሚያረጋግጥ ነው። ይህም ሆኖ የዚህ ሰነድ ይዘት ከፍተኛ የመረጃ ስብሰባ ጥረት ተደርጎ፣ ከፍተኛ ም ርምርና ጥናት ጠይቆ "የተደረሰበት" ምስጢር አይደለም። ከላይ የጠቀምኳቸውን ሁለት ሌላ የጥፋት አጀንዳቸውን ለ ማራመድ ሲሉ የህወሃት መሪዎች ራሳቸው ሆን ብለው ለንባብ እንዲበቁ ወይም ህዝብ ጆሮ እንዲደርሱ ከሚያደርጓቸ ው ስታቲስቲኮች የተለየ ወይም በነሱ ላይ የሚጨምር አንዳችም አዲስ ግኝት የለውም። ይህንን እውነታ እኛ ለቀባሪ ለ ማርዳት በሚገደረደር ሰነድ ይፋ እናድርግ ስንል አክራሪዎቹም ለራሳቸው ፀረ ህዝብ ስትራቴጂ እንደሚያራግቡት ጠን ቅቀን የምናውቀው ነገር ነው።

ከአንድ ከአስራ አራት አመት በፊት የኢህአዴግ መንግስት አየር ሃይል የመጀመሪያ ፓይለቶች ሲመረቁ ምሩቃ ኑ በሙሉ የትግራይ ተወላጆች ብቻ እንደሆኑ በራሳቸው በአየር ሃይል አዛዥ በነበሩት በጄኔራል አበበ ተክለ ሃይማኖት ሲገለፅ፣ በነዚሁ አመታት የኢንቬስትሜንት ባለስልጣን የተባለው ተቋም በየአመቱ ኢንቬስትሜንትን አስመልክቶ በሚያ ቀርባቸው ስታቲስቲኮች በይፋ ለትግራይ ክልል የሚያደሉ እንደሆኑ ሲጠቁም ያኔም እንደ አሁኑ "የአንድ አናሳ ብሄር የ ጭቆና አገዛዝ" ተብሎ ብዙ ሲተችና ሲፃፍ ትዝ ይለኛል። በዚያን ወቅት እስቲ ከዚህ ዘለቅ ብለን እንመልከት በሚል መንፈስ በየሰበሰብው እላቸው ከነበሩትና በፅሁፍም ካሰፈርኳቸው አንዳንድ ነጥቦች መሃከል ዛሬም ቢሆን ከዚህ የተለየ ብዙም የምለው ነገር የለኝምና አንዱን ፅሁፍ በሰፊው ልጥቀሰው።

"የህወሃት ፕሮፓጋንዳ አላማ የትግራይ ህዝብም ሆነ ሌሎች ብሄሮች በመተከል ላይ ያለው በብሄር የተማከለ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ 'በትግራይ ተወላጆች ለትግራይ ተወላጆች' የተተከለ አገዛዝ ነው ብለው እንዲያምኑ የመገፋፋት አላማ ነው። በዚህም መሰረት እየተበጀ ላለው የትግራይ ተወላጆች ኦሊጋርሺ የሚደረገው አድልኦ ሆን ተብሎ አይን እንዲያወጣ ታስቦ በይፋ የሚደረግ አድልኦ ነው። ሰራተኞችና ሌሎች ባለሙያዎች በጅምላ ከስራ እየተባረሩ በትግራይ ተወላጆች ይተካሉ። በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉት መገናኛ ብዙሃን በትግራይ ስለሚደረገው የልማትና የግንባታ እንቅ ስቃሴ፣ በህወሃት አባላትና ደጋፊዎች ባለቤትነት ስለሚቋቋሙ ኩባንያዎች ሪፖርት ሳያደርጉ የሚያልፉ ሳምንታት እም ብዛም ናቸው

" ራሳቸው የትግራይ ተወላጅ የሆኑት የአየር ሃይሉ አዛዥ ለአንድ ለመንግስት ቅርበት ያለው ጋዜጣ በሰጡት ቃለ ምልልስ 'የመጀመሪያው የአየር ሃይል ፓይለቶች ምሩቃን በታሪክ አጋጣሚ በሙሉ ከአንድ ብሄረሰብ ብቻ ናቸው' ሲሉን፣ መንግስታዊ የሆነው የኢንቬስትሜንት ባለስልጣን ከ1983 እስከ 1988 አ.ም. ባለው ወቅት በጠቅላላው በሃገሪቱ ክ ልሎች የተደረገው ኢንቬስትሜንት ቢደመር በትግራይ ከተደረገው ያነሰ ነው ሲለን፣ በዚሁ መንግስታዊ ተቋም ይፋ በ ሚሆኑ ስታቲስቲኮች በነፍስ ወከፍ ኢንቬስትሜንት የተለያዩ ክልሎች ድርሻ ተዘርዝሮ ሲቀርብ የትግራይ ድርሻ 601 ብ

ር ሆኖ የኦሮሞ ክልል 50 ብር ሲደርሰውና የአማራው ክልል ደግሞ እዚህ ግቢ የማትባል 7 ብር ነበረች ስንባል ማንም ቢሆን ይህንን ሁሉ እንደ ተራ ለከፋ (wanton act of provocation) አድርጎ መቁጠር የለበትም።

“ ይህ ሆን ተብሎ የተነደፈ መሰሪ (ማኪያቬላዊ) ስትራቴጂ እንዲህ አይነቱ ቅስቀሳ ሊያስነሳ በሚችለው ‘ፀረ ትግራይ ስሜት’ በመጠቀም የትግራይ ህዝብ ህወሃትን የጥቅሙ ተንከባካቢ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ከቀሩት የሃገሪቱ ብሄሮች ቁጣ የሚጠብቀው ወይም የሚያድነው ብቸኛ ሃይል አድርጎ እንዲያቅፈው የሚጥር ስትራቴጂ ነው። አክራሪዎቹ ይህንን የሚያደርጉት የትግራይ ወገኖቻችንን አስገድደው እጣ ፈንታቸውን ከእነሱ ጋር እንዲያያይዙና ሃገሪቱን ለመግዛት ለመቀጠል ‘ጠንካራ መሰረት’ (strong base) ለመጣል እንደሆነ ግልፅ ነው።” ( **ETHIOPIA: A TRAGEDY IN THE MAKING ADDIS DIGEST N°18 JUNE 1997)**

ይህ የጥቂት አክራሪዎች የጥፋት ስትራቴጂ ገብቶን እሱን ለመዋጋት የህዝቦችን ወንድማማችነት የሚያጎለብት ስትራቴጂ እስካልነደፍን ድረስ “አንድ ብሄር” ሰራዊቱን፣ ፖሊሱን፣ የመንግስት መዋቅሩን፣ ኢኮኖሚውን ሙሉ በሙሉ ቁጥጥሩ ስር አድርጓል የሚለው ቅስቀሳ በቀጥታ የህወሃት መሪዎች ለትግራይ ህዝብም፣ ለቀሩት የኢትዮጵያ ብሄረሰቦችም ለማስተላለፍ የሚፈልጉትን መልእክት ማስተጋባትና የነሱን የቤት ስራ መስራት ይሆናል። ሰሞኑን እንደምንታዘበው ደግሞ የእነዚህን የጥፋት ሃይሎች አጀንዳ የማራመዱ ጉዳይ ከዚህም አልፎ እየሄደ ነው። እንደሚታወቀው እስካሁን ድረስ የህወሃት መሪዎች ‘የትግራይ ህዝብ ብቸኛ ተወካይ ነን’ እያሉ ራሳቸውን ሲያሞካሹ እኛ ደግሞ ከራሳችሁና በጥቅም ከያዛችኋቸው የትግራይና የሌሎች ብሄሮች ጥቂት ተጠቃሚዎች በስተቀር ማንንም የማትወክሉ ጥቂቶች ናችሁ እያልን ስንሞግታቸው ቆይተን ነበር። አሁን የተያዘው አዝማሚያ ከዚህ ጤናማ አካሄድ የወጣ ይመስላል። በዚህ ጉዳይ የግንቦት 7 ንቅናቄ መሪዎች ጁን 4 ቀን በእንግሊዝኛ ባወጡት መግለጫ “አለም አቀፉ ኮሙኒቲ ከህዝቡ 6% ብቻ የሚወክለው ህወሃት የሚከተለውን ፖሊሲ አስከፊ ገፅታ ጠጋ ብሎ እንዲመረምር.....” የሚል ጥሪ በማስተላለፍ እነዚህን ጥቂቶችና የትግራይን ህዝብ ሲያምታቱና ለነዚህ ጥቂቶች የትግራይ ህዝብ ብቸኛ ተወካይነት ሙሉ እውቅና ሲሰጧቸው እናያለን። (Supporting Ethno-centric Policies is Complicity with Ethiopian Governement Crimes Against the Population. June 4, 2009)

እጅግ ግፈኛና ሙሰኛ የሆነ ህብረብሄር ገዥ መደብ እየተተከለ ባለባት አገር ይህንን ችላ ብሎ እንዳለ አንድን ራሱ በጭቆና መዳፍ ስር ያለን ህዝብ ወደ “ገዥ ብሄርነት” ለማሸጋገር መሞከር አደገኛና አጉል አካሄድ ነው። አደገኛ አካሄድ። ምክንያቱም ህዝባችን ከስግብግብነታቸውና ከኪሳቸው ሌላ አለን የሚሉት ብሄርም ሆነ ቆመንለታል የሚሉት ህዝብ የሌላቸው ህብረ ብሄር ገዥዎችን ወደ ጎን ትቶ ከድህነትና ጎስቋላ ኑሮ ለመላቀቅ በአንድነት መቆም የሚኖርባቸውን ሚልዮኖች እርስ በእርስ ሊያናክስ የሚችል አካሄድ በመሆኑ። አጉል አካሄድ። ምክንያቱም የዚህ ገዥ ተብየ ብሄር ህዝብ ያለበትን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጎስቋላ ሁኔታ የሚክድ በመሆኑ።

የትግራይ ህዝብ በኑሮው ከትላንቱ ዛሬ የተመቸው በፖለቲካው መስክስ ከትላንቱ ዛሬ ይበልጥ መብቱ የተጠበቀለት ህዝብ ነው ወይ? አይደለም።

የኢህአዴግ መሪዎች ሃገራችን ዛሬ በአመት ከአስር በመቶ በላይ (double digite) እድገት እያስመዘገበች እንደሆነ ነጋ ጠባ ይለፍፉልናል። ሆኖም የሚደረደሩት አሃዞች ምን ያህል እውነት ቢሆኑ እንኳን ተመዘገበ የሚባለው እድገት የአማራ፣ ኦሮሞ፣ የጉራጌ.....ወዘተና ከነዚህም ይበልጥ ደግሞ አይን በሚያወጣ ሁኔታ ጥቂት የትግራይ ልሁቃን የናጠጠ ሃብት የሚያካብቱበት፣ በሃገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የሃብት መበላለጥ ጣራ የነካበት፣ በሙሰኝነት የተበከለ ለጥቂቶች የተበጀ ደም መጣጭ (predatory) እድገት እንጂ የሃገር ልማት አይደለም። መቀሌና አድዋ የሚሰሩ ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን በቤዛነት እየጠቀሱ እነዚህ ከተሞች እየለሙ የነዚህ ከተሞች ኗሪ እየተመቸው ነው የሚሉ ሰዎች መኖራቸው አይቀርም። ለዚህ መልሱ ቀላል ነው። አዲስ አበባ የሚደረገው የተጧጧፈ የፎቆች ግንባታ ይቺን ከተማችንን በኗሪዎቿ ጉስቁልናና ከአፍሪካ ተወዳዳሪ የሌላትና "The Slum Capital of Africa" ከሚል ስመ ጥፉነት ያላዳናት፣ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ጋር በጎስቋላ ጎጆዎች ሰማይ ጠቀስ ድህነት የሚሰፋፋበት፣ በአለም

ካሉ ዋና ከተሞች በጎስቋላነትና በቆሻሻነት ስድስተኛውን ቦታ ያስያዛት "እድገት" ከአመት አመት እየጨመረ ለሚሄደው ከተሜ ድሃና ጎዳና ተዳዳሪ መፍትሄ እንዳላመጣ ማስታወሱ ብቻ ይበቃል።

አወን እድገት አለ። ግን ደግሞ እድገትና ልማት እየቅል ናቸው። ዛሬ በሃገራችን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ልማት ማለት ከሁሉም ከሁሉም በፊት የርሃብን መቅሰፍት አዙሪት ሰብሮ በሱ ላይ ከአመት አመት የሚልዮኖችን ኑሮ እያሻሻሉ የመጓዝ ሂደት ብቻ ነው። ይህንን አዙሪት አልሰበርነውም። እዚህ ላይ ነው በትግራይ "ልማት" እየተካሄደ ነው የሚሉን ወገኖች ስህተት። ርሃብ በሃገራችን እየከፋ እንጂ እየጠፋ አልሄደም። የትግራይ ህዝብ ደግሞ አማራው፣ ኦሮሞው፣ ወላይታው፣ ሲዳማው ወዘተ እየተራበ እሱ ጠግቦ የሚያድር ህዝብ አይደለም። "ስታቲስቲክሱ" የሚያሳየው ይህ በንጉሱም በደርግም ዘመን 'ከተገቢ ድርሻው በላይ' ይራብ የነበረ መከረኛ ህዝብ ከአስራ ስምንት አመት በስሙ የሚነግደው የህወሃት አገዛዝ በኋላም አስከፊ የሆነ የድህነትና የርሃብ አዙሪት ውስጥ የሚዳክርና "በፐርሰንቴጅ" ሲሰላ አሁንም እንደ ዱሮው ከድርሻው በላይ እየተራበ ያለ ህዝብ እንደሆነ ነው። በዚህ ጉዳይ ከ1983 እ.ም. ጀምሮ ሳያሰልሱ ከአመት አመት ይወጡ የነበሩትን ይህንን ሃቅ የሚያረጋግጡ አሃዞች ወደ ጎን ትተን የርዳታ ማስተባበሪያ ድርጅት በያዝነው አመት ለአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ያቀረበውን የእህል እርዳታ ጥያቄ ብንመለከት የምንገነዘበው ይህንኑ ነው።

በአለፈው ጥር ወር 2001 እ.ም. በቀረበው የእርዳታ ጥሪ በያዝነው አመት "አስቸኳይ የእህል እርዳታ" የሚያስፈልጋቸው ዜጎች ቁጥር 4,945,425 እንደሆነ ተገልጧል። ማነው የት የሚራበው? በሶስት ክልሎች ተወስነን ብንመለከት ከነዚህ ውስጥ 995,095 ርሃብተኞች በአማራው ክልል፣ 683,839 በኦሮሞ ክልልና 674,304 ደግሞ በትግራይ ክልል እንደሚኖሩ እናያለን። ምንም እንኳን በፖለቲካ ስሌት እንዳሻቸ)- አወለጋግደው ይፋ ያደረጉት የመጨረሻው የህዝብ ቆጠራ ውጤት እጅግ አወዛጋቢ ቢሆንም ከሱ ተነስተን በየክልሉ ይኖራል ከሚባለው ህዝብ ስንት ከመቶው ርሃብተኛ እንደሆነ ብንመለከት "ገኘው ብሄር" ከድርሻው በላይ በርሃብ መቅሰፍት እየተገረፈ እንደሆነ እንገነዘባለን። በአማራው ክልል ይኖራል ከሚባለው 20,042,845 ህዝብ 5%ና በኦሮሞ ክልል ከ26,878,482 3.5% ርሃብተኛ ሲሆን በትግራይ ከ4,526,644 ህዝብ 15% ያህሉ ርሃብተኛ እንደሆነ እናያለን።

ይህ አፍጦ አግጦ ያለ ሃቅ በመሆኑ አሌ ሊባል ሳይቻል ሲቀር ሌላ የሚቀርበው "መከራከሪያ" ከጠቅላይ ሚኒስትሩ እስከ ክፍለ ጦር አዛዡ፣ ከየሚኒስቴሮች መምሪያዎች እስከወህኒ ዘበኛው ያሉት የመንግስታዊ ተቋማት ውስጥ የትግራይ ተወላጆች ጎልቶ የሚታይ ቦታ በመያዛቸው ብቻ ይህ ህዝብ "በተወካዩ" ህወሃት አማካኝነት የፖለቲካ ስልጣኑን ጠቅልሎ ይዟል የሚለው መከራከሪያ ነው። ለዚህም "ከተጨባጩ" ስታቲስቲክስ በተጨማሪ እንደ ማስረጃ የሚሰነዘረው ትንታኔ የትግራይ ህዝብ በዚህ መልክ የፖለቲካው ስልጣን ተቋዳሽ በመሆኑ እንደሌሎቹ ብሃሮች ህዝቦች "በፀረ ወያኔው ትግል" የጎላ አስተዋፅኦ ሲያደርግ አይታይም የሚል ክርክር ነው። ይህም በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች የተነሳ የለውን ተጨባጭ ሁኔታ ሳያገናዝብ በጭፍንና በስሜታዊነት የሚሰነዘር የተሳሳተ ክርክር ነው።

አንደኛው በትግራይ ክልልና በቀሩት የኢትዮድያ ክፍሎች ያለው የፖለቲካ ሁኔታ የተለያየ ነው። በሃገራችን በተለይ ከግንቦት ቅልበሳ ወዲህ ከዚያ በፊት በፍንጭም ደረጃ ቢሆን የነበሩት መብቶች ደብዛቸው ጠፍቶ እየተተከለና እየተጠናከረ ያለው አሸባሪና የለየለት የፖሊስ መንግስት (Police State) ነው። ልብ አልነው አላልነው የትግራይ ህዝብ እንደኛ ዛሬ ሳይሆን ገና ህወሃት ሃገራችንን ሲቆጣጠር ጀምሮ በለየለት "የፖሊስ ክልል" ብለን ልንጠራው በምንችለው የአንድ ፓርቲ 'ቶታሊታርያን' አገዛዝ ስር የወደቀ ህዝብ ነው። ዛሬ እኛ ድሮም በቋፍ የነበሩት የመደራጀት፣ የፕሬስ ወዘተ ነፃነቶች ደብዛቸው ጠፋ እያልን ተቃውሟችንን እናሰማለን። ሆኖም ያኔ ድሮ ከምርጫ 97 በፊት በሃገራችን የፕሬስ ነፃነት ፍንጭ በነበረበት ወቅት እንኳን በመላ ሃገራችን ክፍሎች የሚሰራጩት መፅሄቶችና ጋዜጦች በትግራይ ክልክል እንደነበሩ የአደባባይ ምስጢር ነው። ግንቦት 97 ላይ እነ አቶ መለስ "Calculated Risk" ወሰድን ብለው በሃገሪቱ መድበለ ፓርቲ ምርጫ "ፈቅደናል" እያሉ ሲግደረደሩ ታዝበን ነበር። ለትግራይ ህዝብ ግን ይኸም በዛብህ ተብሎ እነ አቶ መለስንና ባለቤታቸውን ጨምሮ የህወሃት ዋና ዋና መሪዎች ከ38ቱ የምርጫ ወረዳዎች በአስራ ሁለቱ ማለትም በአንድ ሶስተኛው ያህል ሌሎች ተወዳዳሪዎች ሳይፈቅዱ ከገዛ ጥላቸው ጋር ተወዳድረው "እያሸነፉ" ለፓርላማ እንደ በቁ አይተናል። ለማነፃፀር ያህል በአማራው ክልል ደግሞ በጠቅላላው ካሉት 138 የምር

ጫ ወረዳዎች ብአዴን/ኢህአዴግ ብቻውን ለምርጫ የቀረበው በሶስት ወረዳዎች ብቻ እንደሆነ እናያለን። የትግራይ ህዝብ እነዚህን ጥቂቶች ባይደግፍ ኖሮ ለምን ከህወሃት ተወዳዳሪዎች ውጭ አንድም ተቃዋሚ አልመረጠም የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። ጥያቄውን በሌላ ጥያቄ "ለመመለስ" ልሞክር።

ነፃ ፕሬስ፣ የመደራጀት መብት ወዘተ ደብዛቸው በጠፉበት የለየለት አፈናና ሽብር ከትግራይ ክልል ዘልቆ መላ ሃገራችንን ባጥለቀለቀበት ሁኔታ አምና በተደረገው የወረዳ ምርጫ የመምረጥ መብት ካለው ህዝብ 93% ድምፅ ሰጥቶ ከጠቅላላው ድምፅ ኢህአዴግ 97% ድጋፍ አገኘ ተብሏል። ምርጫ ቦርዱ የተደረገው "ነፃና ርትአዊ ምርጫ" ነበረ ብሎ ይፋ ባወጣው ውጤት ለአዲስ አበባ ምክር ቤት ከተመደቡት 138 መቀመጫዎች 137ቱን ኢህአዴግ "አሸንፎ" አንዲት ተባራሪ ወንበር ለአንድ የቅንጅት አባል ወድቃለች። በዚሁ በአዲስ አበባ በተደረገው የቀበሌ አስተዳደር ደግሞ በጠቅላላው ምርጫ በተደረገባቸው ቀበሌዎች ያሉትን 2970 መቀመጫዎች አንድም ሳይቀር ኢህአዴግ በሙሉ አፋፍሷቸዋል ተብለናል። በየክልሎቹም ከዚህ የተለየ ስእል የለም። ጥያቄው እንግዲህ ይህ ሁሉ የሆነው ከአዲስ አበባ ጀምሮ በመላ ሃገሪቱ የዚህ ድርጅት ደጋፊዎች ብቻ ለመመረጥ የበቁት የኢትዮድያ ህዝብ ከዳር እስከዳር በኢህአዴግ ደጋፊነት ስለተሰለፈ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ነው። መልሱ ግልፅ ይመስለኛል።

ሁለተኛ ማየት ያለብን ሌላ ቁም ነገር አለ። በዚህ መልክ የመምረጥ እድል ተነፍጎትና ጭብርብርም ተጨምሮበት የክልሉን 38 የፓርላማ መቀመጫዎች ለህወሃት ለማስረከብ የተገደደው የትግራይ ህዝብ ምርጫ ሲኖረውስ ይህንን መብቱን እንዴት ተጠቀመበት? ለዚህ ደግሞ ከዚህ የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ከተተከለበት ክልል ውጭ ያሉ የትግራይ ተወላጆች በምርጫ 97 ወቅት የማያወላዳ ዴሞክራሲያዊና ኢትዮድያዊ መልሳቸውን ሰጥተዋል። እነዚህ ወገኖቻችን ሌላው ቀርቶ በአዲስ አበባ ከተማ ሚዛን ሊደፉ በሚችሉባቸው አካባቢዎች እንኳን ለህወሃት/ኢህአዴግ ተወዳዳሪዎች ድምፃቸውን በመንፈጋቸው ለአዲስ አበባ አስተዳደር ለወሬ ነጋሪነት እንኳን አንድም "ወያኔ" ለመመረጥ ያልቻለበት ሁኔታ ነበር።

የትግራይ ህዝብ "በፀረ ወያኔው ትግል የጎላ ሚና አለመጫወት" የሚባለውን በዚሁ መተው ይቻላል። በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ነገሩን "ጠበብ" በማድረግ የትግራይ ዴሞክራቶችና ልሁቃን በዚህ ለዴሞክራሲ በሚደረግ ትግል የረባ አስተዋፅኦ ሲያደርጉ አይታይም የሚሉ አስተያየቶች ይሰነዘራሉ። ከትግራይ ህዝብ አንፃር በብዛታቸው እዚህ ግቡ የማይባሉ ቢሆኑም ዛሬ እየተተከለ ባለው የስድ ገበያ ኢኮኖሚ ግርግር ተጠቃሚ የሆኑ ቁጥራቸው የማይናቅ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ነጋዴዎች፣ ኢንቬስተሮች፣ ባለሙያዎች፣ የመንግስት ባለስልጣናትና በነሱ ዙሪያ የስርአቱ ተጠቃሚዎች የሆኑ ወዳጆች ዘመዶች እንዳሉ አሌ የማይባል ሃቅ ነው። እየተበጀ ያለው መረን የለቀቀ የህዝብ ደም መጣጭ ስርአት አራማጆችና ተጠቃሚዎች ከየብሄሩ የተውጣጡ ቢሆኑም በዚህ ስርአት ውስጥ የትግራይ ተወላጆች የአንበሳ ድርሻ እንዳላቸው ግልፅ ነው። በትግራይ ውስጥ ይህ ደራሽ ኦሊጋርሺ ምንም ከህወሃት ውጭ ያለ የግል ባለሃብት ሊንቀሳቀስ በማይችልበት ሁኔታ የክልሉን ኢኮኖሚ "በፓርቲ ኩባንያዎች" አማካኝነት ጠቅልሎ የሚቆጣጠር፣ የልማቱንም የእድገቱንም አቅጣጫ ለራሱ ጥቅም እየቀየሰ የሚንቀሳቀስ አጥፊና አደገኛ ክሊክ ነው። ሆኖም የዚህ ኦሊጋርሺ አጥፊነትና እሱንም የመዋጋቱ ጉዳይ አስፈላጊነት እንዳለ ሆኖ አንድ መገንዘብ ያለብን ሌላ ሃቅ አለ። የለየለት ዘረኛነትና ጥላቻ ካልተጠናወተን በስተቀር ከሌሎቹ የሃገራችን ዴሞክራቶች የተለየ ህልምም ሆነ ራእይ የሌላቸው ዴሞክራትና አገር ወዳድ የትግራይ ተወላጆች እንዳሉም መካድ ጨርሶ የሚቻል አይደለም።

እነዚህ ወገኖቻችን በትግሉ ውስጥ የሚያደርጉት ተሳትፎ በተለይ የህወሃት መሪዎች የትግራይን ህዝብ በጉያቸው ለማስገባት የሚያደርጉትን መሰሪ እንቅስቃሴ ለማክሸፍና የትግራይ ህዝብና ሌሎቹ የሃገራችን ብሄሮች እንዲዘፈቁበት የሚፈለገውን የጥላቻና የብሄር ፍራቻ አዙሪት ለመስበር ወሳኝ የሆነ ሚና ሊጫወት የሚችል ተሳትፎ ነው። የህወሃት መሪዎች ፀረ ኢትዮድያ ወንጀል በትግራይ ብሄር ስም የሚፈፀም በመሆኑ እኛ የለም የትግራይን ህዝብ አትወክልም እያልን የምናስተጋባውን ሃቅ የትግራይ ዴሞክራቶች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው "የለም አትዋሽ፣ አትወክለንም" እያሉ ቢያስተጋቡት ይበልጥ ፖለቲካዊና ስነልቡናዊ ትርጉም እንደሚኖረው ምንም የሚያጠራጥር አይደለም። የህወሃት መሪዎች እንዲህ አይነቱ የጎላ ተሳትፎ በጥላቻና በፍራቻ ላይ የገነቡትን ስትራቴጂ እንደ እንቧይ ካብ የሚያፈራርስ በመሆኑ ከጦር ይፈሩታል። በመሆኑም የትግራይን ዴሞክራቶች እኛን በሚያዩበት አይን አይመለከቷቸውም። እኛ ተራ ተቃዋ

ሚዎች ነን። እነሱ ግን "ከሃዲዎች" ናቸው። በዚህ መልክ መፈረጁ በራሳቸው ላይ ብቻ ሳይሆን ዘመድ፣ አዝማድና ወ
ዳጅ ላይ ሳይቀር የሚያመጣው ችግር በቀላሉ የሚታይ ባይሆንም ይህንን ተጨባጭ ሁኔታ አጢኖና ከነሱ ጋር የሰከነና
ቀጣይነት ያለው ውይይት አካሂዶ አንድ የጋራ ስምምነት መድረስ አስፈላጊ ይመስለኛል። ይህንን ካልቻልንና እኛ ከየብ
ሄሩ የተውጣጣን የኢትዮድያ ዴሞክራቶች በጋራ አቁዋም የጋራ ትግል የምናካሂድበት ዘዴ ካላበጀን ከየብሄሩ የተውጣ
ጡ አክራሪዎች ጭቁኖችን በጎሳና በሃይማኖት እያናከሱ የዚህን ሰማእት ህዝብ የሰቆቃ ዘመን የሚያራዝሙበት ሁኔታ
እያመቻቸንላቸው እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል።

እኛ ዴሞክራቶች ከአለው ተጨባጭ ሁኔታና በየብሄሩ ያሉ በዚህ ጥያቄ ለመነገድ ከሚሹ ሃይሎች ጋር በምና
ደርገው ትግል ወንድማማችነትን፣ አንድነትን አንግበን በሰከነና መርህ በተከተለ ሁኔታ በጋራ ልንታገላቸው ካልተነሳን
ቀጣዩና አይቀሬው ትርምስ የዚህ ወይም የዚያ ብሄር ሳይባል ለዴሞክራቶች በሙሉ አስቸጋሪ የሚሆንበትና ከየብሄሩ የ
ተውጣጡ አክራሪዎች ደግሞ ከነጥፋት አጀንዳቸው መሃል መድረኩን ይዘው ሃገራችንን የሚያደሙበት ሁኔታ ይፈጠራ
ል። በህወሃት አክራሪ መሪዎች የትግራይ ህዝብ ሌሎቹን የኢትዮድያ ብሄሮች የህልውናው ጠር አድርጎ እያየ እንዲ
ጠላቸውና እንዲፈራቸው የሚደረገው ጥረት አይቀሬ ውጤት በሁሉም ብሄሮች ውስጥ ላሉና "እኛም የብሄራችን ብቸ
ኛ ተወካይ ነን" ለሚሉና ብሄራቸው የትግራይን ህዝብ እ-ንደ ደመኛ ጠላት አድርጎ እንዲቆጥር ያላሰለሰ ጥረት ለሚያ
ደርጉ ሌሎች አክራሪዎች በሩን በርግዶ መክፈት ነው። የእንዲህ አይነቱ አካሄድ ችግር በሁሉም ብሄሮች ውስጥ ያሉ
ዴሞክራቶች ለአንድነት፣ ለህዝቦች ወንድማማችነት ብሎም ደግሞ ዞሮ ዞሮ ለዴሞክራሲ የሚያደረጉትን ትግል የአቀበ
ት ጉዞ የማድረግ ችግር ብቻ አይደለም። ሜዳውን ለነዚህ አክራሪ ሃይሎች ከተውንና አፀፋ ስትራቴጂ አውጥተን ካል
ተንቀሳቀስን ሰሜቶች መረን ለቀው የሚስፋፉበትና የቦዝንያና ሩዋንዳ አይነት አስከፊ ሁኔታ የሚከሰትበት አደጋ እንዳለ
ግንዛቤ መጨበጥ ይኖርብናል።

ከባዱ፣ ውስብስቡና ህዝባችንን ቀስቅሶና ይዞ የመንቀሳቀስ ነገር በህወሃት የሸብርና የአፈና አገዛዝ ስር እጅግ
አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከዚህ ተነስተን ሲያዩት ቀላል ግን ደግሞ እጅግ አደገኛ የሆነውን የነዚህን የጥፋት
ሃይሎች አጥፊና መርዘኛ ስትራቴጂ የሚያግዝና ወንድም የሆነው የትግራይ ህዝብ "ለካ እውነታቸውን ኖሯል" ወደሚ
ል ድምዳሜ ደርሶ ከጋራው ትግል ጎራ ይልቅ ወደ ፀረ ህዝቦቹ ጉያ እንዲገባ የሚያደርግ ቅስቀሳ የትም አያደርሰንም።
ማንም ዴሞክራት ማንም ኢትዮድያዊ ሃገር ወዳድ ብሎም ማንም
የኢትዮድያ ብሄር ከዚህ የሚያገኘው ምንም ነገር የለምና።

የተያዘው ተጋድሎ ህብረብሄር የሆኑ ጥቂት ፀረ ህዝቦች የተከሉብንን ሙሰኛና ግፈኛ ስርአት እኛም እንደ እነ
ሱ ብሄርና ጎጥ ሳንል በአንድነት ቆመን፣ ብሄርና ጎጥ ሳንል ህዝባችንን በጋራ አንቀሳቅሰን ዴሞክራሲያዊት፣ ፍትሃዊትና
አንዲት በአለም ህዝቦች ሸንጎ አኩሪ ታሪኳ የሚሰጣትን ቦታ የምትይዝ አገር የመመስረት ተጋድሎ ነው። ይህንን ያህ
ል ሰፊና ታሪካዊ ተልእኮ እያለብን በፀረ ህዝቡ ሰፈር ይኸኛው አናሳ ክሊክ ከዚያኛው ፀረ ህዝብ ስብስብ የበለጠ ቦታ
ይዟል፣ ይኸንን ብሄር "እወክላለሁ" እያለ የሚቀጥፈው ቡድን ያኛውን ብሄር "እወክላለሁ" ከሚለው ዋሾ ይበልጥ ድ
ርሻ ተሰጥቶታል የሚል ንትርክ ውስጥ መግባት የለብንም። ነገ በሆነ ተአምር ኢህአዴግ "ዴሞክራሲያዊ" አሰራር ተከ
ትሎ በሰራዊቱም ሆነ በጠቅላላው በመንግስቱ መዋቅር ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ቦታዎች እነዚህ ጥቂቶች ይበልጥ "ፍትሃ
ዊ" በሆነ ዘዴ ሊቀራመቱ ይችላሉ። በዚህ መልክ የየብሄሩ ተወካይ ተብየ "ድርሻ" ይበልጥ ተመጣጣኝ ቢሆን፣ ሌላው
ቀርቶ "ትግራዊው" መለስ ዜናዊ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ነገ ለሆነ የአማራ ወይም የኦሮሞ ተወላጅ ቢለቅ ለኛም ለኢት
ዮድያም ህዝብ የሚያስገኘው ቅንጣት ነገር የለውም። ለዚህ ነው ይህን ፅሁፍ "የህወሃት መሪዎችን ጠበቅ" ከማለት ይ
ልቅ የተያዘው ትግል ምንም እንኳን በአመዛኝ ገፅታው ከነዚህ የጥፋት ሃይሎች ጋር ቢሆንም ከነሱም ዘልቆ በጥቅም የ
ተሳሰሩ ጥቂቶች በታጎሩበት ህብረ ብሄር ስብስብ ላይ ማተኮር ይገባዋል በሚል መንፈስ "የህወሃት/ኢህአዴግን መሪዎች
ጠበቅ" የሚል ርእስ ልሰጠው የፈለኩት።